የሰ/መ/ቁ. 215531

ቀን ፡- ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ታሪኳ ቶሎሳ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ኢትዮጵያ ግርማ

2. አቶ እሸቱ ግርማ

3. ወ/ሮ የሺመቤት ግርማ } ወኪል 5ኛ ተጠሪ ቀረቡ

4. አቶ ዘላለም ግርማ

5. አቶ አዲስ ግርማ፡- ቀረቡ

6. አቶ አባተ ተረፈ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ

ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር የመቃወም አመልካች፤ ተጠሪዎች የመቃወም ተጠሪዎች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ በደብረ ብርሃን ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 167 የሆነ የሟች አባታችን ግርማ አበበ የውርስ ንብረት 6ኛ ተጠሪ ስለያዘ ለቆ ያስረክበን በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን 6ኛ ተጠሪ ንብረቱ በውል ያገኘሁት የራሴ ንብረት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤቱ ክስ የቀረበበት ቤት ከ1ኛ-5ኛ ተጠሪዎች በውርስ የሚገባቸው ንብረት ነው በማለት 6ኛ ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የመቃወም ማመልከቻ ያቀረቡትም ውሳኔው መብቴን ነክቷል በማለት ሲሆን የማመልከቻው ዝርዝር ይዘትም ውሳኔ ያረፈበት ንብረት የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከ1ኛ-5ኛ ካሉት ተጠሪዎች አውራሽ በወኪሉ 6ኛ ተጠሪ አማካኝነት በብር 70,000.00 ገዝቼ ቤቱን ተረክቤያለሁ፡፡ ውሉ ባይመዘገብም ሳያስፈርሱ 10 ዓመት አልፏል፡፡ 6ኛ ተጠሪ ንብረቱን በአደራ እንዲጠብቅ አድርጌያለሁ፣ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል የሚል ነው፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ንብረቱ ለ6ኛ ተጠሪ ተሸጦ የነበረ ቢሆንም ውሉም ስላልተመዘገበ ሚያዚያ 30 ቀን 1988 ዓ/ም በተደረገ ሥምምነት ፈርሷል፡፡ 6ኛ ተጠሪ የገዛሁት ቤት ነው በማለት ተከራክሮ ተረቷል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በሀሰት የቀረበ ነው፡፡ ውክልናው ላይ ያለው ፊርማ የአውራሻችን አይደለም፡፡ በውክልና የተደረገ የሽያጭ ውል ነው ቢባል እንኳን በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት ያልተመዘገበ ረቂቅ ውል ስለሆነ የመቃወም አመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 6ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በውክልና ሥልጣኔ ለአመልካች ቤቱን ሸጬላቸዋለሁ፤ ቤቱን በጠባቂነት ነው የያዝኩት፤ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር ንብረቱ የራሴ ነው በማለት የተከራከርኩት በግንዛቤ ጉድለት ነው ብለዋል፡፡

የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶ 6ኛ ተጠሪ ሕጋዊ ውክልና ከሟች ግርማ አበበ የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ረቂቅ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የቀረበው የመቃወም ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የአመልካች ይግባኝ ማመልከቻን ውድቅ ያደረገ ሲሆን የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ/ም የተጻፈ ሲሆን ይዘቱም በሽያጭ ውሉ መሠረት ገንዘቡን ከፍዬ ቤትና ሠነዶቹን ተረክቤያለሁ፣ በፍ/ሕ/ቁ. 2189 መሠረት የወኪሉ ሥራ ጉድለት ካለበት መቃወም የሚችለው ወካዩ እንጂ ወራሾቻቸው መቃወም አይችሉም፤ ውሉ ፎርሙ አልተሟላም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ወካዩ ባይኖርም ወኪሉ ውሉን ስላመነ፤ ለታመነ ውል ፎርም ሊነሳ አይገባም በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 26887 የተሰጠውን ትርጉም ፍርድ ቤቱ አልተከተለም፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች የሻጭ ወራሾች በመሆናቸው እንደ 3ኛ ወገን ሊታዩ አይገባም፡፡ የሽያጭ ውሉ ፎርሙ አልተሟላም ካሉ ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መቃወሚያ አቅርቤ መታለፉ

ስህተት ያለበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ቤቱን የገዙበት ውል ታምኖ እያለ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት አልተደረገም ተብሎ ክርክራቸው ውድቅ መደረጉ ከፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) እና በሰበር መዝገብ ቁጥር 36887 ላይ ከሰጠው ትርጉም አንጻር ተገቢነቱን ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ውሉን ክደን ነው የተከራከርነው፣ ገዛሁበት ያሉት ውል ረቀቂ በመሆኑ መብት አይሰጣቸውም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ 6ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ለአመልካች በውክልና የተደረገው ውል ስላልተመዘገበ ንብረቱን እኔ እንድገዛው ወራሾች ስለተስማሙ ቤቱን ልረከብ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ለሰበር አቤቱታው መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመረነው ክርክር ያስነሳው ንብረት በደብረ ብርሃን ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 167 ሲሆን ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠረዎች የሟች አባታቸው ግርማ አበበ ወራሾች በመሆናቸው 6ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበው ንብረቱን እንዲረከቡ የተወሰነ ሲሆን አመልካች ባቀረቡት የመቃወም ማመልከቻ ንብረቱን ከሟች አባታቸው በወኪሉ 6ኛ ተጠሪ አማካኝት በብር 70,000.00 ገዝቼ ቤቱን ተረክቤያለሁ፣ ውሉ ባይመዘገብም ሳያስፈርሱ 10 ዓመት አልፏል፤ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት 6ኛ ተጠሪ ሕጋዊ ውክልና ከሟች ግርማ አበበ የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል፣ ነገር ግን አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ረቂቅ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የቀረበው የመቃወም ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ እስከ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ውሳኔውን ያጸናው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን አቤቱታዉ የቀረበዉም፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም (አንቀጽ 58 ይመለከቷል)፣

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ/ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ይሄዉ አዋጅ ነዉ፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ መሠረቱ ውልን መሠረት ያደረገ ሳይሆን የውርስ ንብረትን የሚመለከት ሲሆን አመልካች ውርሱን ለመጠየቅ በሕግ በተመለከተው ጊዜ ክሱን አላቀረቡም የሚል ክርክር የላቸውም፤ የአመልካች ክርክር ውሉን በ10 ዓመት ጊዜ አላስፈረሱም የሚል ነው፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ክስ የውርስ ንብረት መብትን ለማስከበር ንብረቱን የያዘው ሰው ለቆ እንዲያስረክባቸው የቀረበ ዳኝነት እንጂ ውል እንዲፈርስ የተጠየቀ ዳኝነት አይደለም፡፡ ክስ የቀረበበት ንብረት ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በውርስ ያገኙት መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በመቃወም ማልከቻቸው ያቀረቡትን ንብረቱን ከአውራሻቸው ገዝቻለሁ የሚለውን ውል ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር የካዱ በመሆኑ አመልካች ቤቱን በውል በመግዛት ንብረቱ የተላለፈላቸው ስለመሆኑ በሕግ ተቀባይነት ባለው ማስረጃ የማስረዳት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በአመልካች የቀረበው የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ/ም የተደረገው ውል የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በሚደረግበት አኳኋን በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ አመልካች በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል ካላቀረቡ በስተቀር ሕጋዊ የቤት ሽያጭ ውል አለ ለማለት አይቻልም፡፡ በሕግ ፊት ሊጸና የሚችል ውል ስለመኖሩ ካልተረጋገጠ ደግሞ አመልካች ውሉ ሕጋዊና ውጤት ሊሠጠው የሚገባ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 202157 እና ሌሎች መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡ ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-13034 ጥቅምት 15 ቀን 2014 ዓ/ም፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 013-6214 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119663 ሰኔ 18 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ❖ አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሠ/ን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም